# የኢትዮጵያ አገር-አድን ኃይል አቅጣጫ አመላካች ሰነድ

ፌብሯሪ 13 ቀን፣ 2018 ዓ.ም

## መነሻ

በሃገራችን ኢትዮጵያ በፖለቲካ ተቃዋሚው ጎራ የሚገኙ የተለያዩ ድርጅቶችና ስብስቦች ላለፉት 27 አመታት በርካታ ትግሎችን እያካሄዱና አያሌ መሥዕዋትነቶች እየከፈሉ ቢሆንም፤ የተቀናጀና የሚናበብ የትግል ሂደት ባለመኖሩ ምክንያት የሚፈለገው ለውጥ ሊመጣ አልቻለም። የኢትዮጵያ አገር-አድን ኃይል በጃንዋሪ 13 እና 14 ቀን፣ 2017 ዓ.ም በዋሽንግተን ዲሲ በተካሄደው ብሄራዊ የምክክር ጉባኤ ላይ በተሳተፉ 9 ድርጅቶች በይፋ ከተመሰረተ ጀምሮ፤ ለዚህ መሰረታዊ ችግር ዘለቄታዊ መፍትሄ ለመሻት ለአንድ አመት ያክል በስፋትና በጥልቀት ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። የአገር-አድን ኃይሉ በዋነኝነት ካስቀመጣቸው የመፍትሄ ሃሳቦች መካከል ግንባር ቀደሙ፤ በተለያዩ የሃገራችን ክፍሎች በተበታተነና በተናጥል በሚደረጉ ህዝባዊ ትግሎች መካከል መግባባትን በመፍጠር፤ ትግሉ ብሄራዊ ቅርጽ እንዲይዝና ወደ አንድ ግዙፍ የተቀናጀ ህዝባዊ የትግል አቅጣጫ እንዲሸጋገር ማስቻል ነው። ይህንንም እውን ለማድረግ ትግሉን በአንድ ማእከል የሚመራና የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎችን ያለልዩነት ማሳተፍና ማንቀሳቀስ የሚችል ሁነኛ ብሄራዊ ተቋም በአፋጣኝ ማቋቋም ወሳኝ ነው። በመሆኑም እነኝህንና ሌሎች ተያያዥ ጭብጦችን መሰረት በማድረግ፤ የአገር-አድን ኃይሉ ወደፊት ከሌሎች ተመሳሳይ አቋም ካላቸው ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶችና ስብስቦች ጋር በጋራ በመሆን ለሚያዘጋጀው ሁሉን አቀፍ ብሄራዊ ጉባኤ ወይም ሌሎች ስብስቦች በሚያዘጋጁት ተመሳሳይ ጉባኤ ላይ በሚደረግ ተሳትፎ አቅጣጫን የሚያመላክት፤ በዋኝኛነት የኢትዮጵያ ሕዝብን መሰረታዊ መብቶች የሚያረጋግጥና በአለም አቀፍ ህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሚኖረው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን እውን ለማድረግ የሚሰራ ሁነኛ ብሔራዊ የአማራጭ ኃይልን ለማቋቋም የሚያግዝ፤ እንዲሁም በኢትዮጵያ ውስጥ በሰላማዊ ሽግግር "ሁሉን አቀፍ ህዝባዊ የሽግግር መንግስት“ እስኪቋቋም ድረስ በእርሾነት ትግሉን በአንድ ማእከል ለሚያንቀሳቅሰው የአማራጭ ሃይል ግባት የሚሆን የጋራ ሰነድ አዘጋጅተናል።

በአገር አድን ሃይሉ እምነት ዘርና አገር አጥፊው የህወሓት አገዛዝ የአፓርታይድና የቅኝ አገዛዝ ዘዴዎችን በመጠቀም ህዝቡን በዘርና በሃይማኖት በመከፋፈል ሸንሽኖ አገርንና ህዝብን እያጠፋ በመሆኑ መወገድ አለበት። ስለዚህ ሁሉን አቀፍ ህዝባዊ የሽግር መንግስት በኢትዮጵያ ውስጥ እስኪቋቋም ድረስ ትግሉን በአንድ ማእከል የሚያንቀሳቅስና የሚያሸጋግር አንድ አካል መመስረት አለበት። የምስረታ ሂደቱም በኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል ለሚሉ የዴሞክራሲ ሃይሎች ክፍት የሆነ መሆን እንዳለበት በፅኑ እናምናለን። በመሆኑም ይህ እውን ይሆን ዘንድ፤ ፍቃደኛ ከሚሆኑ የተለያዩ ድረጅቶች እና ስብስቦች ጋር በመሆን ሁሉንም የዲሞክራሲ ሃይሎች የሚያሳትፍ የምክክር ጉባኤ ያዘጋጃል። የምክክር ጉባኤው ዋንኛ ትኩረት ትግሉን በአንድ ማእከል ለማንቀሳቀስ ይቻል ዘንድ ከሚከተሉት አልያም ሌሎች መሰል አማራጮች ውስጥ አንዱን (አደራ መንግስት / ብሔራዊ የአንድነት መንግስት / የአማራጭ መንግስት / የአማራጭ ሃይሎች ምክር ቤት / የስደት መንግስት / ወዘተ... ) ለመመስረት ይሆናል። የሚመሰረተው ሁሉን አቀፍ ተቋም የወያኔ ሥርዓት ተወግዶ በኢትዮጵያ ውስጥ የሽግግር መንግስት እስኪቋቋም ድረስ በእርሾነት ትግሉን በአንድ ማእከል የሚያንቀሳቅስ ይሆናል።

## መግቢያ

ኢትዮጵያ አገራችን ከፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ተማግዳ የቆየችበት ወቅት ገደቡን አልፎ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ለመውለድ በቅቷል። ህወሓት መራሹ የኢሕአዴግ አገዛዝ እንዳለፈው ሁሉ ያረጀ ያፈጀ የ26 ዓመት ስልቱን፣ ሃይልና ጭካኔን በመጠቀም ሕዝባዊ እምቢተኝነቱንና አመጹን ለማፈን ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ደረጃ የሞት የሽረት እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል። የሕዝቡ ትግል ግን እየከረረና እየተጠናከረ እንጂ እየተዳከመ አልመጣም። ይህ አዲስ ክስተትና አዲስ የፖለቲካ

አካሄድ አዲስ ምላሽን ይጠይቃል። ይህንንም አዲስ አካሄድና አቅጣጫን ለመንደፍ ሁሉም የሚሳተፍበት የፖለቲካ ሂደት መወጠን ከምንጊዜውም በላይ በጣም አስፈላጊ ነው። ከዚያ ውጭ ግን የህዝብን ጥያቄ በተለመደ መልክ ችላ ብሎ ለመቀጠል መሞከር የበለጠ ትርምስና አቅጣጫውን መገመት ወደሚያስቸግር ቀውስ የሚወስድ ይሆናል።

በሚያሳዝን ሁኔታ አምባገነኖቹ መሪዎች ከተጠናወታቸው የክህደትና የጨለምተኝነት ባህሪ የተነሳ ያለውን ዕውነታ ማገናዘብና መረዳት ተስኗቸው የሕዝብን ተቃውሞና የለውጥ ፍላጎት በአግባቡ ለማስተናደግ የፖለቲካ ፍላጎትም ሆነ ብቃት አይታይባቸውም። ይህንን ማየት ቢችሉ ኖሮ ያለፉበትን መንገድና የሕዝቡን ጥያቄ ባጤኑና በጎ ምላሽም በሰጡ ነበር። በዚህም አካሄዱ የሰላማዊ የስልጣን ሽግግር በር በመዝጋቱ አሁን ወደምንገኝበት ሕዝባዊ አመጽና የትጥቅ ትግል እንቅስቃሴዎች በየቦታው የሚካሄዱበት ወቅት ላይ ተደርሷል። አገዛዙ በበኩሉ ይህንን ሕዝባዊ ተቃውሞና የለውጥ ፍለጋ ትግል ለመቆጣጠር የሃይል እርምጃ በመውሰድ ላይ ይገኛል። ውጤቱ ግን ይበልጥ ስርዓቱን ከድጡ ወደማጡ ከመሄድ አላዳነውም።

አሁን በመሬት ላይ የሚታየው ሃቅ በአገዛዙ ለሃያ ስድስት ዓመት የተካሄደው ተቃዋሚን ሙሉ ለሙሉ ደምስሶ የማጥፋት ስልት የሚፈለገውን ውጤት እንዳላመጣ፤ ሕዝቡ ተደጋግፎ በሙሉ ልብ የሚያካሂደው የመረረ ትግል ማስረጃ ነው። ይህ ክልል፣ ዕድሜ፣ ጎሳና ሃይማኖት ያልገደበው ሕዝባዊ ትግል ያነጣጠረው የሥርዓቱ ዋና አቀንቃኝ በሆነው ህወሓት፣ የሱ አጋር ድርጅቶች፣ እንዲሁም የሥርዓቱ ተላላኪና ጉዳይ አስፈጻሚዎች ላይ ነው። ሥርዓቱ የእኔ ናቸው ብሎ ይተማመንባቸው የነበሩ ተቋማት ሳይቀሩ አሁን ተቃውሚቸውን በግልጽ እያሰሙ መጥተዋል። ቀን በቀን አቅሙ እየዛለ ሥልጣንም ከእጁ እያፈተለከ መውጣቱን የተገነዘበው የገዢ ቡድን የሞት-ሽረት የመጨረሻው የነብስ አድን እርምጃ፤ በቅርቡ ባጠናቀቀው ጉባኤው የይስሙላ የስልጣን ሽግሽግ ለማድረግ አስገድዶታል፤ እንዲሁም በተዘዋዋሪ ከአስቸኳይ ጊዜያዊ አዋጅ የማይተናነስ መመሪያ አሳልፏል። ይህ እርምጃ በአገሪቱ ውስጥ ያለው አለመረጋጋት ከፍተኛ መሆኑን ያመለክታል። ሁሉም እንደሚያስታውሰው ተመሳሳይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ባለፈው አመት ለዘጠኝ ወራት ያህል አውጆ ነበር። ምንም እንኳን ሕዝባዊ አመጹን ለጊዜው ጋብ እንዲል ለማድረግ ቢረዳውም፤ የሕዝብ መሰረታዊ ጥያቄ ባለመመለሱ ተቃውሞው የበለጠ ተጠናክሮ ለመከሰት በቅቷል። ሆኖም ግን አሁንም ይህን የተናጥልና የተበታተነ ህዝባዊ ትግል በአንድ ላይ ለማቀናጀትና ለማስተባበር የሚያስችለውን የአመራር ክፍተት ማሟላት ተስኖታል።

ከ1997 ምርጫም በኋላ በተቃዋሚው ጥንካሬ ማጣትና የእርስ በርስ ሽኩቻ ምክንያት ሕዝብ የሚሻው ለውጥ ሳይገኝ ይባሱኑ የገዢው ሥርዓት እንደገና በሥልጣኑ ላይ ሊያንሰራራ ችሏል። አሁንም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይፈጠር ተቃዋሚው የሕዝቡን ትግል ተከትሎ፣ ጥያቄውንም አዳምጦ፣ በይበልጥም አገራችን ያለችበትን አደገኛ ወቅት ተገንዝቦ የአገርን አንድነት የሚያስከብርና ለሚፈለገው ለውጥ የሚያበቃ የትግል አቅጣጫ መንደፍና የትግሉ አካል መሆን አለበት። በውሃ ቀጠነ ተለያይቶ ወይም ለሥልጣን ጉጉት ተነጣጥሎ መጓዙ በአገራችንና በሕዝቡ ላይ መቅሰፍት እንዲወርድ ወይም ያለው የተጠላ አገዛዝ እድሜ እንዲራዘም እንደመፍቀድ ይቆጠራል።

በአብዛኛው የአገሪቱ ክፍል እየተካሄደ የሚገኘው የወቅቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በመልክና በይዘት የተለያየ አደረጃጀት የያዘ ሲሆን፤ ከቀድሞው የበለጠ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ሕዝባዊ ተቃውሞ የሆነበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ይህ ትግል ይበልጥ የተጠናከረና ለሚፈለገውም ድል እንዲበቃ ለማድረግ ብሔራዊ አደረጃጀት፣ ቅንጅትና ራዕይ ያለው ብልህ አመራር ያስፈልገዋል።

ስለዚህ በዚህ ታሪካዊ ወቅት ሁሉንም የዲሞክራሲ ሃይሎች የመከሩበትና የተሳተፉበት አግላይ ያልሆነ ሂደት በማከናወን ከህወሓት/ኢህአዴግ ሥርዓት የተሻለ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን እውን ለማድረግ የሚያስችል የተማከለ አማራጭ ሃይል በማቋቋም ትግሉን በአንድ ማእከል ከማፋፋም ውጭ ሌላ አማራጭ የለም።

የሚቋቋመውም የአማራጭ ኃይል፤ ላለፉት 26 አመታት ከተደረጉ የትብብር ልምዶች ትምህርት በመውሰድ፤ ጥንካሬያቸውን በማዳበርና ለድክመት ምክንያት የሆኑ ጉዳዮችን በማስወገድ፤ ሀገራችን አሁን የምትገኝበት ሁኔታና ትግሉ የሚጠይቀውን ምላሽ ለማስተባበር ተመጣጣኝ የሆነ አደረጃጀትና ብቃት ያለው አመራር መስጠት ያስፈልጋል። በመሆኑም አስቸኳይ ጉባኤ በማዘጋጀት በምክክርና በመግባባት ሁነኛ የሆነ ብሔራዊ የአማራጭ ኃይል መስርቶ ትግሉን በአንድ ድምጽና ማእከል ማቀናጀት አስፈላጊና ውቅታዊ ግዴታ ነው።

## የትግል አቅጣጫ አመላካች ዋና ዋና ዝርዝር ጉዳዮች

### ሀ. በአገራችን ኢትዮጵያ ከጨቋኙ የህወሓት/ኢህአዴግ ሥርዓት ወደ ዴሞክራሲያዊና ፍትሃዊ ሥርዓት ለማሸጋገር የሚደረገውን ትግል አቅጣጫ የሚያሲዝ ብሔራዊ የአማራጭ ኃይል የመመስረቱ አስፈላጊነት የሚከተሉትን አቤይት ምክንያቶች መሰረት ያደረገ ነው፤

1ኛ. አገዛዙ በሚከተለው የፖለቲካ ልዩነትን በሰላም ለማስተናገድና የተለየ አስተሳሰብን በበጎ ማየት ከማይችል ዕብሪታዊ-ግትርነት ባኅሪ በመነጨ የሚወሰዱ ሕዝብን አግላይና ኃላፊነት-የጎደል የጭካኔ ተግባራትና ፋሽስታዊ ድርጊት እየከፉ መሄዱና የዴሞክራሲ ዋና መገለጫ የሆነዉ የብዙሃን ተሳትፎና ድምጽ ወሳኝነት ቦታ ማጣቱ፣ ሌሎች አገሮች የፕሬስ ነፃነትን ጥቅም ተረድተው ስራ ላይ ሲያውሉ፣ ህወሓት/ኢህአዴግ ጋዜጠኞችን ማሰሩ፣ ከሃገር ማባረሩ፣ የዜጎች የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመሰብሰብ፣ የመደራጀት መብቶችን ሙሉ በሙሉ ማገዱ፣ ባጠቃላይ የህግ የበላይነት ያለመኖሩ።

2ኛ. በገዢው ሥርዓት፤

ሀ) በጋሙጎፋ የኮንሶ ብሄረሰቦችን በልማት ስም መሬታቸውንና ንብረታቸውን በመቀማት ከመኖሪያቸው በመንቀልና በመግደል ከኢትዮጵያ እስከመጨረሻው እንዲጠፉ የዘር ማጥፋት ወንጀል ተፈጽሞባቸዋል።

ለ) በጋምቤላ፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን አኝዋኮች በጭካኔ ተገለዋል።

ሐ) በኦጋዴን፣ ሴቶችና ወንዶች፣ ልጆችና አዛውንቶችን ከመኖሪያ ቀያቸው በማባረር እያሳደዱ ገለዋቸዋል።

መ) በኦሮምውና በሶማሌ ብሄረሰቦች መካከል ችግር በመፍጠርና በማጋጨት፤ በተለይ ደግሞ "የሶማሌ ክልል ልዩ ሃይል" የተባለን ሃይል አደራጅቶ የጥፋት ስልጠና ሰጥቶ የኦሮሞ ህዝብን በማስጨፍጨፍ፤ በቅርቡ ደግሞ ይህንኑ ህወሓት የጠነሰሰውን ፍጅት ለመሸሸ ለዘመናት ከኖሩበት ቀዬአቸው ተፈናቅለው በሃረር ኮምቦልቻ በሰፈሩ ንፁሃን ዜጎች ላይ አሰቃቂ ጭፍጨፋ በማካሄድ፤ ለአያሌ የኦሮሞና የሶማሌ ብሄረሰብ አባላት ሕይወት መጥፋትና ለመቶ-ሽዎች መፈናቀል ምክንያት ሆኗል።

ሠ) በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚኖሩ የኦሮሞ ብሄረሰብ አባላትን መሬት በኃይል በመንጠቅና በግፍ በማፈናቀል በሽዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን ጦም አዳሪ እንዲሆኑ አድርገውታል። በሺዎች የሚቆጠሩትንም በግፍ ገሏል።

ረ) ወያኔ ኢትዮጵያ ውስጥ እስር ቤቶች በሡፊው ገምብቷል። የተገነቡት የእስር ቤቶች ከመጠን በላይ ሞልተውና ተጣበው የሚታዩት በኦሮሞና በአማራ ብሔረሰብ ተወላጅ እስረኞች ነው።

ETHIOPIA

ሰ) ወያኔ ገና ከጥንስሱ በመርሐ ግብሩ ሰነድ ላይ ቀርጾ የተነሳው የአማራውን ሕዝብና የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን በሙሉ በጠላትነት ፈርጆ ከኢትዮጵያ ምድረ ገጽ ማጥፋትነው። የአማራው ሕዝብ በህወሓት ተጨፍጭፏል። ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያክል፤ በወልቃይት ጠገዴ፣ በጎንደር፣ በደብረ ታቦር፣ በጋይንት፣ በባህር ዳር፣ በደብረማርቆስ፣ በቅርቡ ደግሞ በወልድያና በቆቦ እጅግ በርካታ ንጹሃን አማራዎች በህወሓት/ኢህአዴግ ተጨፍጭፈዋል። የአማራው ሕዝብ በተደጋጋሚ በተደረገበት ተከታታይ አማራን ከሚኖርበት ቀዬ የማባረር ዘመቻ፤ ከጋምቤላ፣ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ከደቡብና ከሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች በብዙ ሽህ የሚገመቱ አማሮች ለአመታት ከኖሩበት ቀዬአቸው ቤት ንብረታቸውን ጥለው ተባረዋል። በተጨማሪም የአማራውን ቁጥር ለመቀነስ በተወሰደው ስውር እርምጃ፤ እራሱ የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት እንዳመነው፤ ሁለት ሚሊየን አምስት መቶ ሽህ አማራዎች የት እንደደረሱ እስካሁን አይታወቅም።

ሸ) ወያኔ የኢትዮጵያን መንግስት የሥልጣን እርካብ ከጨበጠ በኃላ ይዞ የመጣውን ዕኩይ የጥፋት ዓላማ በፍጥነት ተግባር ላይ በማዋል በቁጥር መግለጽ የሚያስቸግር በሚሊዮን የሚቆጠሩ የአማራ ሕዝብ ተወላጆችን የተለያዩ የጥፋት ዘዴዎችን በመጠቀም አጥፍቷል፤ ገድሏል። በተለይም በበጌምድር ወልቃይት ጠገዴ፣ በጎጃም መተከል፣በአርሲ አርባጉጉ፤ በወለጋ አሶሳ፤ በሐረርጌ በበደኖ ወተርና አሠቦት ገዳም፣ መነኩሳትና አማራዎች እንደ አራዊት በወያኔና በተባባሪወቻቸው እጅ በግፍ ታርደዋል።ከሞት የተረፉት ከቀያቸው ተፈናቅለው፣ ከመሬታቸው ተነቅለው አገርና ንብረት አልባ እንዲሆኑ ተደርጓል። በአጠቃላይ ወያኔ የዘር ማጥፋት ወንጀል በአማራው ሕዝብ ላይ ፈጽሟል።

3ኛ. በከፍተኛ የሙስና እና የሥልጣን-መባለግ አባዜ የተበከለው የአገዛዝ ጥቂት የገዥዉ ቡድን ቤተሰቦች፣ ግለሰቦች፣ የፓርቲው ተቋሞች ኢኮኖሚውን በሙሉ ቁጥጥር ስለያዙት፣ ነጻ የገበያ ውድድር መጥፋቱ፣ ኢኮኖሚው የፍጆት እቃወችን፣ ምግብን፣ ወዘተ ለማቀርብ አለመቻሉ፣ አቅርቦትና ፍላጎት የሰማይና የምድር ያህል መራራቃቸው፣ ለጥቂት የጎሳ መሪዎች ነን ለሚሉ ቡድኖች (Ethnic elites) ገደብ የለሽ የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት መቆናጠጫ መሆኑና ተጠያቂነት የሌለበት ሙስና እንዲንሰራፋ ማድረጉና ገንዘብ ወደ ዉጭ ለማሸሽ ዋና ምክንያቱ ስርአቱ ራሱ መሆኑ፣ ለህዝብ ኑሮ ተፈላጊ የሆኑ አቅርቦቶች ዋጋቸው አስተማማኝና የተረጋጋ ሊሆን አለመቻሉ፣

4ኛ. ሕዉሓት/ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅሞች የሚጎዱና፣ የተፈጥሮ ሀብቶቿን አሳልፈዉ የሚሰጡ ሚስጥራዊ ስምምነቶችን ከማድረጉ በላይ የኢትዮጵያን ዳር ድምበር ልዕልናዋንና የተፈጥሮ ሐብቷን አሳልፎ ለጎረቤት አገሮች በመስጠት ለወደፊት ኢትዮጵያ ልትወጣው አዘቅጥ ውስጥ መክተቱ።

5ኛ. የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደህዝብ እንደዜጋ በቡበድንም ሆነ በግል የሚያነሷቸዉን ተገቢ ጥያቄዎች አለመመለሱ፣ እንዲያውም፣ጠያቂዎች እንደ ወንጀለኛ እየተቆጠሩ ችግር ላይ መውደቃቸው፣

6ኛ. ወያኔ ለፖለቲካ ፍጆታ ሲል በቤተ እምነቶች ውስጥ ጣልቃ በመግባት ብዙ ወንጀሎች ፈጽሟል። የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መሪዎች እንዲሰደዱ ካደረገ በኋላ አንዴ ሳይሆን ሁለቴ በዘረኝነት ላይ በመመርኮዝ የቤተክርስቲያኗን ሃላፊ የትግራይ ተወላጅ አድርጓል። የሙስሊሙን ሕብረተሰብን እምነቱን በመናቅ ከሊባኖስ አህባሽ የተሰኘ አንጃኛ በማስገባት በምእመናኑ ላይ ከመጫኑም በላይ ሕብረተሰቡ የመረጣቸውን መሪዎቹን በፀር-ሽብርተኝነት በመወንጀል ከርቸሌ አስገብቷቸዋል።"

7ኛ. ንጹህ ኢትዮጵያዊያንን ለመወንጀል እንዲያመች “የጸረሽብርተኛ” ህግ ደንግጎ፣ አገሪቱን ወደ “እስርቤት” መለወጡ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚከራከርለት ነጻ የሆነ የማህበራዊ ድርጅት እንዳይኖረዉ፣ የመንግስት ያልሆኑ ተቋማትን እንቅስቃሴዎች የሚገድብ ህግ አውጥቶ ከስራ ላይ ማዋሉ፣ የፕሬስ ነፃነት ሙሉ በሙሉ እንዲታቀብ ማድረጉ፣

8ኛ. የሕዉሀት/ኢሕአዴግ ህገ መንግስት በሚፈቅደው መሰረት የተደራጁና በሰላማዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ድርጅቶች በተከታታይ ህልውናቸው እንዲጠፋ መደረጉ፣ መሪዎቻቸውና አባሎቻቸው በግልጽና በድብቅ መታፈናቸዉ፣ መገደላቸው፣ በይፋ ባልሰሩት ወንጀል መታሰራቸው፣ መሰደዳቸውና የመድብለ ፓርቲ ሚና ፍጹም በሆነ ደረጃ መጥፋቱ፣ በዚህም ከህወኃት/ኢሕአዴግ ሌላ ድርጅት ወይም ሕብረት በሃገሪቱ ውስጥ ምንጊዜም ስልጣን ሊይዝ ወይም ሊጋራ እንዳይችል ያላሰለሰ የአፈና ዕቅድ፤ የስለላ መረብ መዘርጋቱና የሽብር ተግባር ማከናወኑ፤

9ኛ. በተጭበረበ ተደጋጋሚ የምርጫ ትርኢት ህወሓት/ኢህአዴግ ፍጹምነቱን በማሳየት፣ ምርጫ በሚካሄድበት ዓለም ውስጥ ታይቶ በማያውቅ ደረጃ 100 % ድምጽ አግኝቻለሁ ብሎ የአለምን ሕብረተሰብ ማጭበርበሩና የአንድ ፓርቲ አምባገነንነትን ፍጹም ማድረጉ።

10ኛ. ህወሓት/ኢህአዴግ አዲስ የትምህርት ፖሊሲ በሚል ጥራት የሌለው ትውልድን ተስፋ ገዳይ ፖሊሲ እና አድሏዊ የሆነ የፖለቲካ፣የኢኮኖሚና የማሕበራዊ ሥርዓት ለወጣቱ ትውልድ እድል ፈጣሪ ባለመሆኑ፣ የተማረው ወጣት እጣ ፈንታ ድንጋይ መካብና ስደት መሆኑ፣ ስደተኞች በሚሄዱበት ሁሉ ክብራቸው መገፈፉ፣ ህይወታቸው ለአደጋ መዳረጉ፣

11ኛ. የወያኔ አገዛዝ በተከተለው መሠሪ የፖለቲካ መሥመር ኢትዮጵያውያን ተለያይተው እንዲያድጉ በተገደዱበትና እራሳቸውን እንደ-አንዲት-አገር-ዜጋ ሣይሆን በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ኪሣራ የአካባቢ ማንነታቸው አይሎ እንዲወጣና እሱም ላይ እንዲያተኩሩ በሆነበት፤ በተከታታይ ምርጫ ለማሸነፍ ሲል የመንግስት ሰራተኞች፣ ተማሪዎች፣ ገበሬዎችና፣ ሴቶች የፓርቲ አባል እንዲሆኑ፣ ከመንግስት በጀት እየመደበ ከማስገደዱም በላይ "አንድ ለአምስት" በተሰኘ የስለላ፣ የአፈናና የቁጥጥር መረብ ዘርግቶ የገዥዉን ፓርቲ አባላት ወደ ስድስት ሚሊዩን እንዲደርስ ማድረጉ፣በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎችን ያለፈቃዳቸው አባል እንዲሆኑ ማስገደዱ፣

12ኛ. ቋንቋን መሰረት ያደረገው ፌደራላዊ አወቃቀሩ ዴሞክራሲያዊና የራስን አስተዳደር ለማጎልበት ሳይሆን፤ ያፓርታይድ ያገዛዝ ዘዴን በመጠቀም የህወሓትን ቡድን የበላይነት ለማረጋገጥ፤ ብሔራዊ አንድነትን ለመበታተንና ዜግነት ላይ የተመሠረተ የሃገር ልዑላዊነትን ለማዳከም መሆኑ፤

13ኛ. የአገሪቱ ዕጣ-ፈንታ ላይ አሉታዊ ጫና ሊያሳድር በሚችል መልኩ ብዙ ባዕዳን የየራሣቸውን ከጊዚያዊ ጥቅማ-ጥቅም ጀምሮ የረጅም-ጊዜ-ትልምን (ስትራቴጅካዊ ጥቅምን) ለማስጠበቅ እጆቻቸውን እስከ ክንዳቸው የዘፈቁበት ሁኔታ መፈጠሩ፤

14ኛ. የኢትዮጵያን አንድነት፣ ሉአላዊነት፣ ደህንነቷንና ሐብቷን ለአደጋ መዳረጉ፣ ይኽ ሁሉ ደግሞ በአገራዊ አንድነትና በኢትዮጵያዊ ማንነት ላይ ያላሰለሰ ዘመቻ በመደረጉ ምክንያት፣ የኢትዮጵያዊነት መንፈስና የአገራዊ-አንድነት ስሜት በእጅጉ በተሸረሸሩበት፤ አጠቃላይ ሁኔታ በመሆኑ ነው።

## ለ. የወቅታዊው ሁኔታንና ተከታታይ ሕዝባዊ እንቅስቃሴውን የተለየ ከሚያደርጉት ምክንያቶች በከፊል የሚከተሉት ናቸው፤

1ኛ. ካለፉት አራት ዓመታት ጀምሮ በተለያየ መልክ ህዝባዊ እንቅስቃሴና እምቢተኝነት እየሰፋና እየጎመራ መምጣት ሤአኔን በቃኝ ማለቱ።

2ኛ. የኢትዮጵያዊያን እስላሞች የመብት ጥያቄና እንዲሁም አገዛዙ በክርስትና በእሰልምና እምነት ተቋማት ውስጥ ጣልቃ አይግባ የሚሉና ተመሳሳይ ጥያቄዎች መቀጠላቸው።

3ኛ. በኦሮሞ ማህበረሰብ የመሬት ነጠቃና ከይዞታ ማፈናቀል ሳቢያ የተነሳው ከፍተኛ ህዝባዊ ተቃውሞና የመብት ጥያቄ አይሎ ስርአቱን በቃኝ ማለቱ።

4ኛ. በአማራው ማህበረሰብ በተለይም በጎንደርና በጎጃም በወሎ ወዘተ.. የተነሳው ህዝባዊ እንቅስቃሴ በአንዳንድ አካባቢዎች በነፍጥ ጭምር የታገዘ ተጋድሎ ሲያካሂድ ከአንድ አመት በላይ ማስቆጠሩና ሕዝባዊ ዐመጹን ማፋፋሙ፤

5ኛ. በነጠላና በጋራ እየተቀጣጠሉ ያሉ ህዝባዊ አመጾች የለውጥ ፍላጎትንና ትግል የሚገልጹ ሂደቶች ስለሆኑ።

6ኛ. በአዲስ አባበም ሆነ በተለያዩ ከተሞች ፍትህዊ ያልሆነውን የግብር ጫና በመቃወም የንግዱ ህብረተሰብ የመረረ ትግል በማካሄድ በስርአቱ ላይ ያለውን ተቃውሞ በግልጥ ማሳየቱ

7ኛ. ሀገሪቷን ለመከፋፈልና ህዝቡንም ለማበጣበጥ ያመቻል በሚል ስሌት ሀገሪቷን ያካለለበትና የሚያስተዳድርበት ቋንቋን መሰረት በማድረግ በተሸነሸነው ፌዴራሊዝም የተነሳ ቅጥ አንባሩ በጠፋው ድንበር አማካይነት ትንኮሳዎች እየተደረጉ ተከታታይ ግጭቶች መፈጠራቸውና ህይወት መጥፋቱ። ቤትና ንብረት መውደሙ። ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ ከቀዬው እንዲባረርና እንዲሰደድ መደረጉ።

8ኛ. በዋንኛነት ቋንቋንና ኃይልን በመጠቀም የተደረገው የድንበር ክለላና ሽንሸና ሲሆን በዚያ ምክንያት የተነሳውን የህዝብን አመጽ ያስቆምልኛል ወይም አቅጣጫ ያስቀይርልኛል ብሎ በማሰብ በህወሓት በእራሱ ከክልል አስተዳደር ጋር በመተባበር በህዝብ መኸከል ግጭት መፍጠር ነው። በቅርቡ በኦሮሚያና በሱማሌ ክልል የተከሰተው አሳዛኝ ክስተት ለዚህ የጥፋት ሂደት እንደ ምሳሌ ሊጠቀስ የሚችል ነው። (በዚህ ባሰለፍነው ወር ብቻ በመቶዎች የሚቆጠር ሕዝብ ባሰቃቂ ሁኔታ ተጨፍጭፏል፣ በሺዎች የሚቆጠር ንብረት ወድሟል፣ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ከሚኖርበት ተፈናቅሏል) ቀደም ሲል ተመሳሳይ ሁናቴዎችም በሌሎች ክልሎች ተከስተዋል። ያም ሆኖ በተቃራኒው ግን ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች ያስገኙዋቸዉ ዉጤቶች አበረታች ናቸው።

9ኛ. ከሁለተ አሥርተ ዓመታት በላይ የተሰበከውን የመለያየትና የጥላቻ ፖለቲካን ግንብ አፍርሰው የኦሮሞ ህዝብ ደም ደሜ ነው በማለት ጎንደርና ጎጃም የአንድነት ደወል ደወሉ ። የኦሮሞ ቄሮዎች አማራ ኬኛ ጣና ኬኛ ብለው ዘመሩ። ወደ ጎጃምና ጎንደርም አንድነታቸውን ለመግለጽ ተመሙ።

10ኛ. የኦሮሚያ ክልል አዲሱ አስተዳደር ወደ ጎንደርና ጎጃም ተጉዞ ኢትዮጵያዊነትን ከፍ ባለ ድምጽ ዘመረ። የኦሮሞና የአማራ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ሁሉም ኢትዮጵያዊ አንድ ነው ሲሉ የጥንቱን የጥዋቱን መሠረት ገሃድ አወጡት። ኢትዮጵያ የምንኖርባት የጋራ ሀገራችን ብቻ ሳትሆን ከጠላት ለማዳን መስዋዕት በመክፈል በጋራ የተቀበርንባት ወደፊትም የምንቀበርባትም ነች አሉ። ያ የጥላቻ ግንብ ጨርሶዉኑ ተደረመሰ ባይባልም በተግባር ግን መፈራረስ ጀመረ።

11ኛ. ስለዚህም ትግሉን አጠናክሮ ለመቀጠል ተስፋ ሰጭ ሂደቶች ተከስተዋል። በቀውስ ውስጥ የሚገኘውና ከንዱም በተወሰነ ደረጃ እየላላ የመጣው ህወሓት በአመራሩ ውስጥ ክፍፍሉ ቀጥሏል።የተወሰኑትን የአመራር አባላት አባሮ የተወሰነ አንጃ የአመራሩን ሥልጣን ለብቻው በእጁ ለማስገባት እየሞከረ ነው።

ETHIOPIA

12ኛ. እንደ ዱሮው ክልሎችን ወይም የኢህአዴግ ድርጅቶችን ለመጫን የነበረው ኃይል በተወሰነ ደረጃ የተዳከመ ይመስላል።

13ኛ. በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች አገዛዙ ሲያካሂድ ከቆየው ግድያና ግፍ በተጨማሪ ከላይ የተጠቀሱት በቅርቡ የተፈጸሙት ጭፍጨፋና ወንጀል፤ ሥርዓቱን በውስጥና በውጭ ይበልጥ አጋልጦታል። ይደግፉት የነበሩትም አንዳንድ መንግሥታት ጥያቄ እያነሱበት ነው።

14ኛ. እነዚህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት የሕዝቡን ትግል ጥንካሬና የሥርዓቱን እየተዳከመ መሄድ ያበስራሉ። ህዝብም በስርአቱ ላይ እምነቱ ሙሉ በሙሉ እንደተሟጠጠና በህወሓት/ኢህአዴግ ስር ለመገዛት በፍጹም እንደማይሻ እያሳየ ነው። ሆኖም ግን ሥርዓቱ አሁንም የከህደት፣ የማጭበርበር፣ የሰለቸና የተጋለጠ ፕሮፓጋንዳውን በማስተጋባት፣ ለለውጥም እንደተነሳ በማስመሰል የሕዝቡን የትግል ስሜት ለማኮላሸትና ትጥቅ ለማስፈታት እላይ ታች እያለ ይገኛል። በህወኃት ውስጥ ባለፉት ሳምንታት ይፋ ያደረገው ሹም ሽርም የዚሁ መሰረታዊ ለውጥ ያደረገ የማስመሰል አካሄዱ አንድ አካል ነው። በቅርቡ የህወሓት፡-መራሹ የኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ ስብሰባ ከተካሄደ በኋላ ለሕዝብ ይፋ የሆነው አሳፋሪ የማላገጥ ተግባር የስርዓቱን የውስጥ ጭንቀትና በስልጣን ላይ ለመቆየት ከምንም ነገር ወደ ኋላ እንደማይል ያስመሰከረበት ነው።

ከላይ ባጭሩ የተዘረዘሩትን ችብጦችና አደጋዎች መሰረት በማድረግ ከተቃዋሚው የሃይል አሰላለፍ ጋር ሲነጻጸር፤ ብቃት ያለው ሁሉንም ያሰባሰበ ብሔራዊ-አማራጭ ባለመኖሩ ከፍተኛ ክፍተት እንዳለ መገንዘብ ያስፈልጋል። በአገሪቱ ላይ ያንዣበበው አደጋ እንዳይከሰት ለመግታት አደጋ ቢከሰት እንኳ ችግሩ እንዳይባባስ ለመቆጣጠርና በአጭር ለመቅጨት የሚያስችል ደረጃ ላይ መገኘት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። የህዝብንና የሃገርን አንድነት የሚበትንና የሚያወድም ተግባር ለማስቆምና ሀገርን እንደ ሀገር ለማስቀጠል ከምንጊዜዉም በላይ የዴሞክራሲ ኃይሎች ተሰባስበው አንድ ማዕከል ፈጥረው ብቃት ያለው አመራር ማደራጀት ጊዜ የማይሰጥ ጉዳይ ነው። የሕወሓት የሽብርና የግፍ አገዛዝ ዕድሜ የሚኖረውና በኢኳያውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰቆቃ ሊቀጥል የሚችለው፤ አገር-ወዳዱ የዴሞክራሲ ኃይል ከተለመደው አስተሳሰብና አደረጃጀት ተላቅቆ፤ እንዲሁም ከጠባብ የቡድንተኝነትም ሆነ የድርጅት አጥር ወጥቶ አገርንና ሕዝብን መታደግ የሚችል አዲስ አገርንና ህዝብን ያስቀደመ ብሔራዊ የኃይል አሠላለፍ መያዝ ካቃተው ብቻ ነው።

## ሐ. ውስጣዊና ውጫዊ አደጋዎች

ኢትዮጵያዊነትን ማእከል ያላደረገ የብሄረተኛ ድርጅቶች መጠናከር አደጋ፤

ይህ አሁን የተጀመረውን እንቅስቃሴና የህዝብ መነሳሳት ለማፈን ህወሓት/ኢህአዴግ የሚወስደው የግፍ እርምጃ ባብዛኛው በቋንቋ ማንነት ላይ የተመሰረተ ነው። ይህ ደግሞ ብዙዎችን በማንነት ላይ ባተኮረ አመለካከትና አካሄድ እንዲገፉበት ያበረታታል። በአንድ በኩል መብት ረጋጩ በዘር ላይ የተመሰረተ አገዛዝ በሆነበት የጥቃት ኢላማ የሆነው ክፍል ደግሞ ከትውልዱ፣ ከቋንቋ ማንነት ጋር በተያያዘ ምክንያት መሆኑ በቀላሉ ኢትዮጵያዊነትን ማእከል ያላደረገ የአክራሪ ብሄረተኛ ድርጅቶች ሰለባ እንዲሆን ያደርገዋል። በቋንቋ ማንነት ላይ አተኩሮ የሚደረግ እያንዳንዱ የጅምላ ጥቃት ብሄረተኞችን እያጠናከረ እንደሚሄድ የሌሎች አገሮች ተሞክሮ እንዲሁም የህወሓት እንቅስቃሴና የእድገት ታሪክ ብዙ ያሰተምረናል።

## መ. የእርስ በርስ ግጭት አደጋ

የህዝባችን የአብሮ መኖር፣መዋለድ ወዘተ እሴት እንዳለ ሆኖ ከላይ የተገለጸው ሁኔታ በጊዜው በመገንዘብ አደጋውን መቀነስ ካልተቻለ እጅግ አደገኛ የሆነ የእርስ በርስ ግጭትን በሀገራችን ውስጥ ሊጋብዝ ይችላል። ይህ የህዝብ እርስ በርስ ግጭት

በሕወሀት/ኢህአዴግ ወይም በተቃዋሚ ውስጥ በማንነት ላይ የተመሰረተ ግጭት ቢካረር እንጠቀማለን ብለው በሚያስቡ ክፍሎች ወዘተ ተንኳሽነት ሊቀሰቀስ ይችላል። በተጨማሪም ሀገሪቱ በማያበራ የእርስ በርስ ግጭት እንድትዘፈቅ የሚሹ የውጭ መንግስታትም፣ በአባይ ዙሪያና በገልፍ መንግስታት በኩል የሚያንዣብበውን አደጋ ግምት ውስጥ ስናስገባ የዚህ አይነቱን እኩይ ተግባር ለመቀስቀስ ወደ ኋላ እንደማይሉ መገንዘብ ተገቢ ነው::

በተጨማሪም፤

1ኛ. ወያኔ/ኢህአዴግ  ያሰፈነው ሥርዓት ሆን ብሎ በጥናት ሀገሪቱንና ህዝቡን በዘውግና በእምነት.... ወዘተ ከፋፍሎት በመገኘቱ።

2ኛ. ለ26 አመት በሰፈነው የዘውግ ፖለቲካ አመለካከት የተነሳ ሁሉም ወደየራሱ ዝቅተኛ ማንነት ጥያቄ ላይ እንዲያተኩር ተደርጎ እነሆ በገዢው ሰርአት የሚደገፍ እኛና እነሱ በሚል ጎራ የመከፋፈል አስተሳሰብ የህብረተሰቡ የግንኙነት መሰረት እየሆነ በመሄዱ፤ ይህ ክፍፍል እጅግ ስር እየሰደደ ህብረተሰቡም ከጊዜ ወደ ጊዜ ልዩነቱ በተካረረ ግጭት መልክ በመከሰት ላይ በመገኘቱ።

3ኛ. አገዛዙ በሀይማኖት ጉዳይ ጣልቃ መግባት ብቻ ሳይሆን ለመቆጣጠር በሚያደርገው ሩጫ ለእምነት ነፃነት የቆሙትንም በማሰርና በማሳደድ፣ የሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ ተከታታይ ጥቃት መፈጸሙና እውነተኛ የሀይማኖት ነፃነትን የሚሹትን የማዳከም ጥረቱን መቀጠሉ።

4ኛ. በክርስትና ሀይማኖት ተከታዮች በኩልም የአገዛዙ ጣልቃ ገብነት እጅግ ሰፊ አደጋ እንዲጋረጥ ማድረጉና የኦርቶዶክስ ቤተክርስትያንም አመራር ከሁለት እንዲከፈል ማድረጉ።

5ኛ. ለረዢም ጊዜ የቆየውና ከአገዛዝ ወደ አገዛዝ ተላልፎ አሁን እጅግ ገዝፎ የምናየው አስተዳደራዊ በደል፣ አድሎና ዜጎችን ከስብዕና የወረደ ግፍ የፈጠረው ምሬትና ብስጭት መፍትሄ ሳያገኝ ከችግር ላይ ችግር እየጨመረ አሁን ወዳለንበት የተወሳሰበና የሀገሪቱን ህልውና እየተፈታተነ ወዳለ አደጋ ላይ መጣሉ።

6ኛ. የሀገሪቱ ሰራዊት አመራር በአብዛኛው ከአንድ ግንባር ፓርቲና ከአንድ ዘውግ የተውጣጣ፣ ታማኝነቱም በዋናነት ለዚሁ ድርጅት መሆኑ ህወሀት/ ኢህአዴግ በመሀል አገር ወይም በሌላ ቦታ ሽንፈት ቢገጥመው ሊከሰት የሚችለው መራራ ግጭት፣ ሰፊ መሆኑ።

7ኛ. በሀገሪቱ እንዲንሰራፋ የተደረገው የዘውግ ፖለቲካ በሠራዊቱ ውስጥም ስር እየሰደደ መምጣቱ፣ በሰራዊቱ ይዞታ ላይ የሚፈጠር ነውጥ የሰራዊቱን አባላት በየዘውግ እንዲከፋፈሉ የማድረጉና ወደ ጎሳ ጦርነት የመግባቱ አደጋ በመኖሩ

8ኛ. ክልል ተብለው የተሰየሙት እስተዳደር ክልሎችም የየራሳቸው ፖሊስ ሰራዊትና ሚሊሻ የመሰረቱ ሲሆን ታማኝነታቸውም ቢሆን በዋናነት፣ ለመለመላቸው፣ ደመወዝ ለሚከፍላቸውና የፖለቲካ አባል ላደረጋቸው ለክልላቸው የዘውግ ድርጅት መሆኑ። የየክልሉ ፖሊስ ሰራዊትና ሚሊሻም በቀላሉ ወደ ተዋጊ ሀይልነት ሊቀየር የሚችልበት ሁኔታ እጅግ ሰፊ መሆኑ።

9ኛ. ዜጎች ላለፉት 26 አመታት በጎሳቸው/ በሚናገሩት ቋንቋ ምክንያት እንዲዋረዱ የሆነበት፣ ከቦታ እንዲፈናቀሉ የተገደዱበት ሁኔታ ሰፊ በመሆኑ፣ በጎሳየ/ ብሄረሰቤ ምክንያት ተጠቅቻለሁ የሚሉበት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ያንድ ጎሳ አባላት ልዩ ተጠቃሚ ሆነዋል የሚለው ስሜትም እጅግ ጎልቶ ስለሚገኝ። ይህም አደገኛ ወደሆነ ግጭት ለማምራት እንደሚችል በመገንዘብ፡



ETHIOPIA

10ኛ. ሀገራችን ላለፉት 50 አመታት ያለፈችበት የፖለቲካ ሂደት እጅግ ሰፊ ግጭትን፣ ሞት፣ የንብረት መውደምን፣ የቤተሰብ መለያየትን፣ መፈናቀልን ወዘተ አስከትሏል። በዚህ ሄደት ያልተነካ ሰው አለ ለማለት አይቻልም። ይህም በመሆኑ እጅግ ሰፊ ቂም በቀል፣ የስነ-ልቦና ቁስል ወዘተ ህብረተሰባችንን በማሰቃየት ላይ መሆኑ። እነዚህን ሁሉ አያይዘን ስንመረምር የሀገራችን ፖለቲካ እና ማህበራዊ ጉዳዮች እጅግ አሳሳቢ በሆነ መልኩ ተወሳስበው የሚገኙበት ሁኔታ ላይ እንደምንገኝ፣ ኢትዮጵያዊነት ራሱ በብዙ ጥያቄና አጣብቂኝ ውስጥ እንደገባ የህዝባችንም አንድነት እጅግ መሰረቱ እየተናጋ እንደሆነ አዳዲስ አደጋዎችም እየተከሰቱ እንደሆነ እንገነዘባለን። ይህ እጅግ የተወሳሰበ ሁኔታ ሀገሪቱ ወዳልታሰበ ግጭት፣ እልቂትና ምናልባትም ሊፈጠር በሚችለው የቀውስ አዙሪት ሕልውናዋ አደጋ ላይ ሊወድቅ የሚችልበት እውነታ ሊከሰት እንደሚችል ያልተጋነነ ስጋት አለ። የህወሓት አገዛዝ የችግሩ አንዱ አካልና ዋናው ምክንያት በመሆኑ ይህን ሁኔታ በራሱ ሊቀይረው ከቶውንም አይችልም፡፡ እንዲያውም እየቆየ በሄደ ቁጥር የሚወስዳቸው እርምጃዎች ችግሩን ወደባሰ መወሳሰብ ያሳድገዋል። በሌላ በኩል ከሚነሱት ብሶቶችና ጥያቄዎች ውስብስብነት አንጻር ሲታይ አንድ ድርጅት በተናጠል ሁሉንም ሊያረካ የሚችል ልዩ መፍትሔ ሊያመጣ አይችልም። ከዚህም በላይ እንደዚህ የተወሳሰበ ችግርን መፍታት የሚቻለው አንዱ መፍትሄ ሰጭ ሌላው ደግሞ መፍትሄ ተቀባይ ሆነው ሳይሆን ሁሉም የችግሮቹ ባለቤት ሁሉም ደግሞ የመፍትሄዎቹም ባለቤት ሲሆኑ ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን፣ ፍትህን፣ መተማመንና፣ አርቆ አሳቢነትን መሰረት አድርጎ ያለፉ ችግሮች እንደገና እንዳይደገሙ ምን መደረግ እንዳለበት መግባባትና መስማማት ላይ መድረስ ሲቻል ነው። ይህ ማለትም ማንንም ያላገለለ ሁሉም ባለድርሻዎች የሚሳተፉበት የብሄራዊ መግባባትን መሰረት ያደረገ የሽግግር ሂደትን መወጠንና እውን ማድረግን ይመለከታል።

ስለዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን እና ተያያዥ ጉዳዮችን መሰረት በማድረግ የኢትዮጵያ አገር-አድን የቀውጢ-ጊዜ ግብረ-ኃይል አባል ድርጅቶች ተመሳሳይ አቋም ያላቸውን ሌሎች ድርጅቶች በማካተትና ከሌሎች ተመሳሳይ የዲሞክራሲ ስብስቦች ጋር ምክክር በማድረግ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚሻውንና ዴሞክራሲአዊ ሥርዓትን እውን ለማድረግ የሚያስችል እንዲሁም ለአለም አቀፉ ህብረተሰቡም በኢትዮጵያ ውስጥ የተረጋጋና ሰላማዊ ሽግግርን እውን ለማድረግ እንደሚቻል የሚያረጋግጥ ሁነኛ ብሔራዊ የአማራጭ ኃይል ለማቋቋም የጉባኤ ዝግጅት ሂደትና ዘመቻ በአስቸኳይ ለመጀመር ወስነናል። በተናጠልም ሆነ እንደስብስብ ሌሎች በሚካሄዱ ጉባኤዎች ላይ የምናደርጋቸው ተሳትፎዎች እነኚህን ጭብጦች መሰረት የሚያደርጉ ይሆናሉ።

## ሠ. አደጋን የታደገ ሰላማዊ ሽግግር እንዲካሄድ ወሳኝ ቅድመ ዝግጅቶች፤

አሁን ሀገራችንና ሕዝባችን ከሚገኙበት ሁኔታ ለመውጣት የሚከተሉት አምስት ነጥቦች መሰረታዊ ናቸው ብለን እናምናለን፣

1ኛ. ሁሉንም የዲሞከራሲ ሃይሎች የሚያሳትፍ የምክክር ጉባኤ ማዘጋጀት።

2ኛ. የምክክር ጉባኤው ዋንኛ ትኩረት ትግሉን በአንድ ማእከል ለማንቀሳቀስ ይቻል ዘንድ ከሚከተሉት አልያም ሌሎች መሰል አማራጮች ውስጥ አንዱን (አደራ መንግስት / ብሔራዊ የአንድነት መንግስት / የአማራጭ መንግስት / የአማራጭ ሃይሎች ምክር ቤት / የስደት መንግስት / ወዘተ… ) መመስረት

3ኛ. መረጋጋትን ለመፍጠር ሃቀኛ፣ አስተማማኝ፣ ሁሉን አሳታፊ፣ በሁሉም ተቀባይነት ያለው የፖለቲካ ሂደት መጀመር፣

4ኛ. ሁሉንም ባሳተፈ ውይይት የቀውሱን መንስዔ አስወግዶ ለሕዝቡ ጥያቄ መልስ ለመስጠት የሚችል የሽግግር ሂደት ማካሄድ፣

ETHIOPIA

5ኛ. ጠንካራ መሰረተ ያለው ሂደት ተግባራዊ በማድረግ ዘላቂ የሆነ ለውጥና የዴሞክራሲ ስርዓት መዘርጋትና ተመሳሳይ ቀውስ ወደፊት እንዳይከሰት መስራት፤

## ረ. ከአመጽ ይልቅ አመጽ አልባ የሆነ ሽግግር ወቅቱ የሚጠብቀው ተግባር ነው

ከላይ የተጠቀሱትን እውን ለማድረግም የሚከተሉት አብረው የሚታዩ ተጓዳኝ ተግባሮች ናቸው።የሚቻል ቢሆን የሰው ሕይወት ሳይጠፋ፣ የአገር ንብረትና ሃብት ሳይወድም በሰላማዊ መንገድ ለውጥ ቢመጣ የሚጠላ የለም። ይህም በመሆኑ ሰላማዊውን ሽግግር የሚመርጥ ሁሉ ለተግባራዊነቱ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፤ አሁን ግን በአገዛዙ ጀብደኝነትና ጭካኔ የተሞላበት አካሄድ ሁኔታው ይበልጥ እየተካረረና ህዝቡም ሌሎች አማራጮችን እየወሰደ፤ ከቁጥጥር እየወጣ በመሄድ ላይ ነው።  የወቅቱ ሁኔታ ከቀውስ የጸዳ፣ ሁሉን ያቀፈና ያሳተፈ፣ ዴሞክራሲያዊ የሆነ፣ የፖለቲካ አቅጣጫን ይሻል። ሕዝቡ ያለውን ስርዓት አንቅሮ ተፍቶታል። ለተመሳሳይ አምባገነን አገዛዝም እንደማይመች ይፋ አድርጓል።

የሚያስገርመው ጉዳይ አሁንም የቀውሱ ባለቤት የሆነውና በሥልጣን ላይ ያለው ቡድን እራሱን ብቸኛ የሰላም፣ የመረጋጋት፣ የእድገትና የልማት፣ የእኩልነትና የዴሞክራሲ ፈጣሪና አውታር፣ ሕዝብም ከዳር እስከዳር የሚደግፈውና የሚከተለው አድርጎ ማቅረቡ ነው። በአጭሩ አገዛዙ የሚከተለው መንገድ አገሪቱን ከተዘፈቀችበት የቀውስ ማእበል የሚያወጣ ሳይሆን በቀውስ ላይ ቀውስ እየወለደ የኤኮኖሚና የማህበረሰብ ውድመትን የሚያስከትል መንገድ ነው። ከዚያ ማዕበል ለመውጣት ያለው መንገድ አንድ ብቻ ነው። ሁሉን ያሳተፈ አዲስ ሰላማዊ የሽግግር ሂደት መጀመር። አሁን ያለውን ሁኔታ በኢትዮጵያ ውስጥ የተረጋጋ ስርዓትን ለማምጣት በህዝብ ተቀባይነትና ከበሬታን ሊኖረው ወደሚችል መንግስትና ስርኣት መሸጋገሯ የግድ ነው። ህወሀት መራሹ አገዛዝ ሙሉ በሙሉ የህዝብን አመኔታና ክብር አጥቷል።

## ሰ. የኢትዮጵያ አገር-አድን ኃይል ከላይ የተዘረዘሩትን ጭብጦች መሰረት ያደረገ አስቸኳይ የምክክር ጉባኤ ለማዘጋጀት መርሃ ግብር ነድፏል።

## ሸ. የኢትዮጵያ አገር-አድን ኃይል፤ የትግል ራእይ

ህዝብ የስልጣን ምንጭና ባለቤትነቱ የሚያረጋግጥባት፤ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩባት፤ዜጎች በእኩልነት፤ በመፈቃቀድና በመተሳሰብ አብረዉ የሚኖሩባት፤ ሀገራዊ አንድነቷ የተረጋገጠባት፤ የተለያዩ ባህል፤ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶች የሚከበሩባትና የሚበለጽጉባት፤ የመድበለ ፓርቲ የፖለቲካ ሥርዓትና ተሳትፎ የሚረጋገጥባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መመስረት ነው።

## ቀ. የኢትዮጵያ አገር-አድን ኃይል፤ የጋራ ተልኮዎች

የህወሓት/ኢህአዴግ ዘውግ ተኮር አድሏዊ የክልል አገዛዝን በማስወገድ የኢትዮጵያን አንድነት ሉዓላዊነትና የዜጎችን ሰብዓዊ መብት የሚያስከበር ሁሉን አቀፍ ሕዝባዊ የሽግግር መንግስት በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲቋቋም፤ ከሌሎች የአንድነትና የዲሞክራሲ ሃይሎች ጋር አማራጭ ሃይል በማቋቋምና ቅድመ-ሁኔታዎችን በማመቻቸት፤ አምባገነንነትን ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ከኢትዮጵያ ተወግዶ፣ እዉነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ለማድረግ እና ህዝብ የስልጣን ባለቤት እንዲሆን፣ የህግ የበላይነት እንዲከበር በጋራ መታገል ነው፡፡

ETHIOPIA

ስለዚህ፤

1ኛ. ሀገራችን ያለችበትን ሁኔታ ለውጦ ዴሞክራሲያዊ ሁኔታዎችን ለመፍጠር፣ በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ የተጠናከረና የተቀናጀ ትግል ማድረግ ያስፈልጋል። በሀገር ቤት የተደራጀ ህዝባዊ ትግል በማድረግ ያለውን አምባገነን ሥርዓት ከውስጥ መታገልና መነቅነቅ የሚያስፈልግ ሲሆን፤ በውጭ ደግሞ የተጠናከረና የተቀናጀ ዲፕሎማሲያዊና ተዛማጅ ትግሎችን በማድረግ የሥርዓቱን የፋይናንስና የዲፕሎማሲያዊ ድጋፉን ማድረቅ ያስፈልጋል። እነዚህን ሁለት የትግል ዘርፎች  በውል ለማድረግ ደግሞ በበቂ መደራጀትን ይጠይቃል። በይፋም ይሁን በኅቡእ ተደራጅተው የሚታገሉ የፖለቲካ ሃይሎች፣ እነዚህን ሁለት የትግል ዘርፎች አጣምረው መታገል ይጠበቅባቸዋል። በማደራጀትም ረገድ በሀገር ውስጥም ይሁን፤ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን የማደራጀት ሃላፊነት አለባቸው።

2ኛ. ለሥርዓት ለውጥ የምናደርገው የመጀመሪያው መሠረታዊ እርምጃ አንጥረን ባወጣናቸው የጋራ ራዕይና ዓላማዎች ዙሪያ በውጭ የሚገኘው የተከፋፈለና የተዳከመው ሠፊውን ህዝባዊ የተቃዋሚ ጎራ አንድ ላይ በማሰለፍና በማቆም በሚፈጠረው የትግል ኃይል፣ በአገር ውስጥ የሚካሄደውን የሕዝባዊ እምቢተኝነት ብሄራዊ ቅርጽ ይዞ የትግል ማዕበሉ በስፋት እንዲቀጣጠል ማገዝና ለድል እንዲበቃ ማድረግ ናቸው።

## በ. የኢትዮጵያ አገር-አድን ኃይል፤ መሰረታዊ የእምነት መርሆዎች

1ኛ. በኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነት፤ የሕዝቡ የሥልጣን ባለቤትነትና ሉዑላዊነት እንዲሁም በሃገሪቱ የግዛት አንድነት ላይ ግልጽና የማያወላውል ዕምነት መኖር፤

2ኛ. የማንኛውም የኢትዮጵያዊ ግለሰብ ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶችን ማክበር፤

3ኛ. በድርጅቶች ውስጥና በምንሰባሰብበት የጋራ ማዕቀፍ ዲሞክራሲያዊ ግንኙነቶችንና አሰራሮችን ለማስፈን መስራት፤

4ኛ. በኢትዮጵያ ውስጥ የህግ የበላይነት እንዲኖር መታገል፤

5ኛ. በኢትዮጵያ ህዝብ መካከል ምንም ዓይነት አድሏዊነት እንዳይኖር፤ ሁሉም በሕግ ፊት እኩል ዜጎች መሆናቸውንና ማንም ከህግ በላይ ያለመሆኑን ማመንና በተግባር ማስረገጥ፤

6ኛ. የህወሓት/ኢህአዴግ ስርዓት ዘረኝነት አሸባሪና አምባገነናዊ ብሄረተኛነት የተጠናወተው፣ ግፈኛ፤ አፋኝና መሰሪ ስርዓት በመሆኑ መለወጥና በዲሞክራሲያዊ  ሥርዓት መተካት እንዳለበት ማመን

7ኛ. እውነተኛና ዘላቂ የሆነ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት አግላይ ያልሆነ፤ ሁሉን አቀፍ ሰላማዊ የሽግግር ሂደት እንዲኖር ከባለድርሻ አካሎች ጋር ቅድመ-ሁኔታዎችን ለማመቻቸት፤ በጋራ መስራት ናቸው።

## ተ. የኢትዮጵያ አገር-አድን ኃይል፤ የሚያቀርቡት አማራጭና  ሊከተሏቸዉ የሚገቡ የትግል ስልቶች

1ኛ. ከላይ የተዘረዘሩትን ዓበይት ችግሮችን ለመፍታት እንዲሁም መሠረታዊና አስተማማኝ ለዉጥ ለማምጣት የዲሞክራሲ ኀይሉ አሰላለፉን አቀናጅቶ ሕዝባዊ እንቅስቃሴና ትግሉ ብሔራዊ ቅርጽ ያለው  ትግል ለማካሔድ ሁነኛ የብሔራዊ አማራጭ ኃይል_ማቋቋም።

ETHIOPIA

2ኛ. በአማራጭ ሃይል አማካኝነት የተባበረ ትግል በማድረግ በሥልጣን ላይ ያለዉን አስከፊና ዘረኛ ሥርአት አስወግዶ ዘላቂነት ያለዉ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት ሰላማዊ ሽግግር በማድረግ "ሁሉን አቀፍ ህዝባዊ የሽግግር መንግስት በኢትዮጵያ ውስጥ ኢንዲቋቋም በጋራ መታገል።

### ቸ. የኢትዮጵያ አገር-አድን ኃይል፤ በማጠናከር ለውጤት የሚያበቁ ተጨባጭ እርምጃዎች

1ኛ. በዓበይት ችግሮችና በመፍተሔ ሃሳቦች ዙሪያ የዓላማ አንድነት እንዲፈጠር ሰፊ ዘመቻ በመጀመር ህዝባዊ መሰረት ማስያዝ

2ኛ. የአቅም ግንባታ

3ኛ. በአገር ቤት የሚካሄደው ሕዝባዊ ትግል ቅርጽ ይዞ በማያቋርጥ ሁኔታ እንዲካሄድ ሰፊ ዘመቻ ማካሄድ፤ የሥልት፣ የቴክኒክ፣ የገንዘብ፣ የቁሳቁስ፣ የስልጠና፣ የዲፕሎማሲና የሞራል ድጋፍ ማድረግ።

4ኛ. ለዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ አስፈላጊ የሆኑትንም ሁለንተናዊ ቅድመ ዝግጅቶች ማፋጠን።

5ኛ. በአገር ዉስጥና ከአገር ዉጭ ያሉ ድርጅቶች የሠመረ ግንኙነት ማድረግ፣መጣር

6ኛ. የዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ እውቅና፤ ድጋፍ እንዲኖር ማስቻል

### አለም አቀፍ ድጋፍን ማሰባሰብ

አሁን ባለው ሁኔታ አለም አቀፉ ህብረተሰቡ ሌላ ምስቅልቅሉ የወጣ ሀገርን በምስራቅ አፍሪካ ማየት አይፈልግም፡፡ ስለዚህም አገር-አድን ኃይሉ ከሌሎች ተቃዋሚዎች ጋር ሆኖ መረጋጋትን በቀጣይነት ሊያሰገኝ እንደሚችል ማረጋገጥ ይኖርበታል። ከዚህ አኳያ ድጋፍ የማሰባሰብ ሂደቱ በብሄራዊ መግባባትና በሰላማዊ መንገድ በሀገራችን ውስጥ የሥርዓት ለውጥ ሊመጣ የሚችልበት ሁኔታና ተቃዋሚውን አቅም በመገንባት አኳያ የተቃኘ ማድረግ ተገቢ ይሆናል። በዚህ አኳያ አሁን የተጀመረውን ጥረት ይበልጥ አጠናክሮ መቀጠል ያሻል።

ይህ ኃይል ከላይ የተጠቀሱትን ሁሉ ለብቻው ለመፈጸም አቅሙ አይፈቅድለትም.ስለሆነም ከሁሉም በፊት በራእይ ደረጃ ህብረተሰቡም ሆነ የተለያዩ ድርጅቶች ይህን እቅድ እንዲቀበሉት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል። ከዚህ በተጨማሪ ከድርጅቶች ጋር ውይይት በማካሄድ ይህ ሰነድ ይበልጥ እንዲዳብር ማድረግ ያሰፈልጋል።

በተጨማሪም ከፖለቲካ ድርጅቶች ባሻገር ሌሎች ተቋሞችም (ለምሳሌ ዩኒቨርሲቲ፣ የምርምር ተቋሞች፣ተደማጭ ግለሰቦች፣ የሀይማኖት ተቋሞች ወዘተ) በዚህ አጀንዳ ዙሪያ ተከታታይ ውይይት እንዲያደርጉ በማበረታታት አጠቃላይ ሂደቱ ህዝብን ያሳተፈና ህዝብ የታቀፈ እንዲሆን ጥረትይደረጋል።

## ማጠቃለያ

ከላይ እንዳቀረብነው ሀገሪቱ የምትገኝበትን ወቅታዊ ሁኔታና የሕዝብ ብሶት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በመገምገም፤ በሀገራችን የተንሰራፋውን አምባገነናዊ ሥርዓት የማስወገድን አስፈላጊነትና ይህንንም ማከናወን ዛሬ የሚታየውን የሃይል አሰላለፍ በማጤን፤ በተቃዋሚ ድርጅቶች በኩል እስከዛሬ ካልተሟሉት፣ በተለይም ለአንድ አላማ በአንድነት ቆሞ በአንድ ቃል

ለመናገር ያለመቻልን፣ ይህ ሰነድ ማዕከሉ ካደረጋቸው ነጥቦች ውስጥ አንዱና ዋነኛው በማድረግ የጋራ ኃይሉ ለዚህ ጉዳይ መሟላት ቅድሚያ ሰጥቶ እንደሚሰራ በሙሉ ልብ ያረጋግጣል።

ኢትዮጵያችንን ከብተና እና ሕዝባችንንም ከተደገሰለት የእስ- በርስ ትርምስ አደጋ ለመታደግ የኢትዮጵያውያን አገር-ወዳዶችና የአንድነት ኃይሎች አገራዊ ጉባዔ በአስቸኳይ በማዘጋጀት ብቃት ያለው ብሔራዊ አማራጭ ኃይል እንዲፈጠር የሚያስችል ፈጣን ሂደት ለመጀመርና ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴው ተጀምሯል።

ከዚህ በተጨማሪ የሽግግር ወቅት ወሳኝ ጊዜ መሆኑን አጥብቀን እናምናለን። ካሁኑ ዝግጅት ካልተደረገ በሌሎች ሀገሮች እንደታየው ለውጥ ቢመጣም የመጣውን ለውጥ እንደ ህወሓት ባሉ መሳሪያ ያነገቱ አምባገነኖች የስልጣን መወጣጫ እንደሚያደርጉት አያጠራጥርም። ሀገራችን ወደ መልካምም ይሁን መጥፎ አቅጣጫ ልትጓዝ የምትችለው በዚህ ወሳኝ የሽግግር ወቅት በሚፈጠሩ ክስተቶች ይሆናል። በመሆኑም በሽግግር ወቅት የሽግግር መንግስት ሊመራበት የሚገባውን ቻርተር ህዝብ ተወያይቶበትና መክሮበት ሊያጸድቀው ይገባል። ከአሁኑ ተወያይተንበትና ተማምነንበት ያጸደቅነው ሰነድ ወያኔ በፈጠራቸው የዘር፤ የሃይማኖትና የኢኮኖሚ ልዩነቶች ሊደርሱ የሚችሉ አለመግባባቶችን ስለሚያስወግዱ ቻርተር አርቅቆ ካሁኑ ለህዝብ ይፋ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው።

ስለዚህ የኢትዮጵያ አገር-አድን አማራጭ-ኃይል፤

1ኛ ይህን አቅጣጫ አመላካች ሰነድ፤ ለሕዝብ ይፋ በማድረግ ሁሉን አሳታፊ አገራዊ ጉባዔ እስኪደረግ ተከታታይ ዘመቻዎች ያካሂዳል።
2ኛ ከዚህ በተጨማሪ ረቂቅ የቻርተር ሰነድ በቅርብ ለህዝብ ይፋ ይደረጋል።

## ማስታወሻ

ከጃንዋሪ 13 እስከ 14 ቀን፣ 2017 ዓ.ም በዋሽንግተን ዲሲ ሁሉን-አቀፍ የምክክር ጉባዔ በዘጠኝ የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች መካከል በተደረገው ውይይት ላይ በተደረሰው ስምምነት መሠረት፤ 1ኛ/ የአገር አድን የቀውጢ ጊዜ ግብረ ኃይል ማቋቋማችን፤ 2ኛ/ ሁነኛ የአንድነት ኃይሎች አማራጭ በአጭር ጊዜ የማውጣት ሂደት ላይ የሚሠራ አንድ ልዩ ኮሚቴ እንዲሰየም መወሰናችንን በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን ይፋ እነዳደረግን የሚታወስ ሲሆን፤ ይህን የኢትዮጵያ አገር አድን-ሃይል አቅጣጫ አመላካች ሰነድ በሙሉ ስምምነት ይፋ የምናደርገው የድርጅቶች ስም ዝርዝር የሚካተለው ነው፤

1ኛ. ሞረሽ ወገኔ የአማራ ድርጅት

2ኛ. ቱሳ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት

3ኛ. የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ንቅናቄ ሕብረት

4ኛ. የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሽግግር ምክር ቤት

5ኛ. የኢትዮጵያ ወጣቶች ብሄራዊ ንቅናቄ

6ኛ. የአማራ ዳግማዊ አርበኞች ንቅናቄ

ETHIOPIA